# <u>የኢትዮ - ካናዳውያን የዲሞክራሲ ፎረም በኦታዋ - ካናዳ</u>

## <u>የድጋፍ መግለጫ</u>

በጀነራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ለበርካታ የትግል ዓመታት ያራምድ የነበረውን ከኢትዮጵያ የመገንጠል አጀንዳን በመተው ለሁሉም የኢትዮጵያ ዜጎች መብት ፤ እኩልነትና ነፃነት መከበር እታገላለሁ በማለት ታህሳስ 22 ቀን 2004 ዓም ያወጣውን መግለጫ የኢትዮ ካናዳውያን የዲሞክራሲ ፎረም በኦታዋ - ካናዳ በደሥታ የተቀበለው መሆኑን ይገልፃል ።

ፎረማችን በአገራችንና በህዝባችን ላይ የወደቀውን የግፍ አገዛዝ በማስወገድ በምትኩ አገራዊ አንድነቷ የተጠበቀ ፤ የህዝቧ እኩልነትና የህግ የበላይነት የተረጋገጠባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመስረት በሚደረገው ትግል ውስጥ የትግሉ አካል በመሆን የሚጠበቅበትን የዜግነት ግዴታ ለመወጣት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል ።

በመሆኑም ፎረማችን የአገርና የህዝብ ጠላት የሆነውን ህውሃት/ኢህአዴግ በኢትዮጵያችን ውስጥ እያደረሰ ያለውን ዘርፈ ብዙ ግፍና በደል በተለያዩ መድረኮች አጋልጠናል ፤ ኢትዮጵያን ለመታደግ በአንድነት ጥላ ሥር በመሰባሰብ ላይ ያሉትን የፖለቲካ ድርጅቶች ፤ ሲቪክ ማህበራትና ታዋቂ ግለሰቦችን ያካተተ አንድ ጠንካራ ህብረት እንዲመሰረት የሚደረገውን ጥረት በመደገፍ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ለመስጠት ይህ ፎረም ቃል ይገባል ።

በማከልም ይህንን በጄነራል ከማል የቀረበውን የኢትዮጵያዊነትን ጥሪ ባለመቀበል በተፃራሪነት የቆሙ የፖለቲካ ድርጅቶች በኢትዮጵያውያን ህብረት ላይ የሚያካሄዱትን አሉታዊ ቅስቀሳ በመተው አቋማቸውን አስተካክለው ህዝባዊውን እንቅስቃሴ እንዲቀላቀሉ ጥሪያችንን እናቀርባለን ።

ፎረማችን አሁንም እነ ጀነራል ከማል የወሰዱትን አቋም ከልብ እየደገፈ ጊዜው የግድ የሚለውን የጋራ ትግል እንዲጀምሩልን አደራ እንላለን ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com